# እ.ኤ.አ ከ ኖቬምበር 21-30/2017 የነበረው


# የአየር ሁኔታ ግምገማ

በኖቬምበር ሶስተኛው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ የተስተዋለ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪም በጥቂት የጋምቤላ፣ የቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ የጅማ፣ የምሥራቅና የምዕራብ ወለጋ፣ የአርሲና የባሌ ኪስ ቦታዎች፣ የደቡብ ኦሞ፣ የሲዳማ፣ የጌዲዮና ቤንች ማጂ እንዲሁም የመካከለኛውና የደቡብ ትግራይ ዞኖች ኪስ ቦታዎች ቀላል መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል የማለዳውና የሌሊቱ ቅዝቃዜ በተጠናከረባቸው ደጋማ ቦታዎች ላይ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች መጠን ያለው ቅዝቃዜ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስ ያህልም በደበረ ዘይት 3.2፣ በአዲስ አበባ ቦሌ 3.5፣ በአደሌ 5.0፣ በአዲግራት 2.5፣ በሀሮማያ 1.6፣ በአምባ ማርያም 3.8፣ በባቲ 4.9፣ በደብረብርሃን 0.2፣ በፊቼ 4.2፣ በኮፈሌ 5.0፣ በሾላ ገበያ 3.6፣ በወገል ጤና 3.5፣ በእምድብር 5.0 መመዝገቡን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡


ባለፉት አሥር ቀናት የነበረው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ5-60.3 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ በጥቂት የደቡብ ትግራይ፣ የደቡብ ጎንደርና የፓዊ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ኢሉአባቦራ፣ ጅማ እንዲሁም ጥቂት የምዕራብ ወለጋ ምስራቃዊው ክፍልና የአርሲ ዞኖች፤ የጋምቤላ ዞን 2 እና አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች ከ2-7 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 1 እና 2) ።

በአሥሩ ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር ጥቂት የደቡብ ትግራይና የፓዊ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ኢሉአባቦራ፣ ጅማ እንዲሁም ጥቂት የምዕራብ ወለጋ ምስራቃዊው ክፍልና የአርሲ ዞኖች፤ የጋምቤለ ዞን 2 እና አብዛኛው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 3)።


ካርታ1   ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ2   ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ3   እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች    መደበኛ    ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21-30/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ

በኖቨምበር ሶስተኛዉ አሥር ቀናት በጥቂት የጋምቤላ፣ የቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ የጅማ፣ የምሥራቅና የምዕራብ ወለጋ፣ የአርሲና የባሌ ኪስ ቦታዎች ፣የደቡብ ኦሞ፣ የሲዳማ፣ የጌዲዮና ቤንች ማጂ እንዲሁም የመካከለኛውና የደቡብ ትግራይ ዞኖች ኪስ ቦታዎች ለጥቂት ቀናት አነስተኛ ዝናብ ያገኙ ቢሆንም፤ በአብዛኛው የሃገሪቱ ቦታዎች ላይ ብዙውን ጊዜ ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ  የአየር ሁኔታ ተዘውትሮባቸዋል። ይህም በመሆኑ የክረምት ተጠቃሚ የሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች የበጋ ወቅታችው ስለሆነና በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሄዱ በአንዳንድ  ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባው አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ለጥቂት ቀናት የተገኘው አነስተኛ እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩ እንዲሁም ደግሞ ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት አዎንታዊ ተፅእኖ ነበረው። በተመሳሳይ ሁኔታ በደቡብ ምዕራብ የነበረው እርጥበት  በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታ እንደነበረው እሙን ነው። በአንጻሩ ደግሞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ዝቅተኛ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው በመሆኑ፤ የተገኘውን እርጥበት በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት አሉታዊ አስተዋጽኦ እንደነበረው ይገመታል (ካርታ 4)።


ካርታ 4   እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2017 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## **እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21-30/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ**

እ.ኤ.አ 21-30 ኖቨምበር 2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ የተሻለ እርጥበት በጥቂት የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ተስተውሏል$ ይህንን ተከትሎ በጥቂት የላይኛው ባሮአኮቦ፣ የታችኛው ስምጥሸለቆና የታችኛው ኦሞጊቤ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት አግኝተዋል$ በሌላ በኩል መጠነኛ እርጥበት በደቡብ ምእራብ ተፋሰሶች ላይ ተስተውሏል፡፡ በዚህም መሠረት በጥቂት የላይኛው ተከዜ፣ የላይኛው ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው የአባይ ደቡባዊው ክፍል፤ የላይኛው ስምጥሸለቆ፣ መካከለኛው የኦሞግቤና የገናሌዳዋ ምዕራባዊው ክፍል ደረቃማ የነበሩ ሲሆን፤ የተቀሩት የሰሜን፣ የሰሜን ምእራብ፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የደቡብና የደቡብ ምስራቅ መካከለኛው ተፋሰሶች በደረቅ ሁኔታ ስር ቆይተዋል (ካርታ 5)$

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 21 እስከ 30/2017 ድረስ በተፋሰሶች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10/2017 የሚኖረው

## የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በአሁኑ ጊዜ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየታየ ያለው የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ በሚቀጥሉት አሥር ቀናትም ቀጣይነት እንደሚኖረው እና ከዚሁ ጋርም ተያይዞ በተለይም በአንዳንድ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የሌሊቱ እና የማለዳው ቅዝቃዜ ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚችልይጠበቃል። በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በተለይም በደቡብ ምዕራብ ኦሮሚያ ባሉ ጥቂት ሥፍራዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ከመጠበቁ በስተቀር በተቀሩት የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ፀሐያማና ደረቃማ የአየር ሁኔታ እንደሚሰፍንና በተለይም በአንዳንድ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚጠናከር ይጠበቃል።

## እ. ኤ. አ ከዲሴምበር 1-10/2016 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የዲሴምበር የመጀመሪያዉ አስር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚጠናከር የሚጠበቅ ሲሆን፤ እንዲሁም በጥቂት ደጋማ ቦታዎች ላይ ውርጭ ሊከሰት እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ:: ይህም ደረቅ ሁኔታ የእድገት ጊዜያቸውን ለጨረሱ እንዲሁም ለመሰብሰብ ዝግጁ የሆኑ ሰብሎችን ለመሰብሰብ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን፤ አርሶ አደሩ እና የሚመለከታቸዉ አካል የደረሱ ሰብሎችን መሰብሰብ ይኖርባቸዋል:: በሌላ በኩል በተዳከመ ሁኔታ ቢሆንም በደቡብ ምዕራብ ኦሮሚያ ጥቂት አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለያየ ምክንየት ዘግይተው ለተዘሩትና የእድገት ጊዜያቸውን ላልጨረሱት የመኸር ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ አቅርቦት ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሩና ለከፊል አርብቶ አደሩ አከባቢዎች ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሟላትና ለእፅዋት ልምላሜ መሻሻል ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡

## ኢ. ኤ. አ ከዲሰምበር 1-10/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት ውስጥ በአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቆይ ትንበያው ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ጥቂት የላይኛው ባሮአከቦና የመካከለኛው ኦሞጊቤ አዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተቀሩት የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ፣ ነፋሻማና ፀሃያማ ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረው ተጠቁሟል። በመሆኑም በብዙዎቹ ተፋሰሶች ላይ ያለው የበጋ የአየር ሁኔታ የውሃ ሀብት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ስላለው ውሃን ለብክነት ከሚያጋልጡ ነገሮች መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን እንጠቁማለን፡፡